ያባዬን ወደ እማዬ

ይህ በሂል -አማርኛ ቋንቋ መናገር በሚችሉ ኢትዮጵያውያን ሁሉ የተለመደ አባባል ነው ። ግማሹ ከአፍ መፍቻ ቋንቋው፤ ከፊሉ ከአማርኛ ሥራዓተ ትምህርትና ከማህበራዊ ሕይወት ግብብነት- ከአፍ ወደ አፍ በመተላለፍ የተገበየ እውቀት ነው። አባባሉ ማህበረሰባችን ለመጥፎ ምሳሌነት ነው የሚጠቀምበት። ሰዎች የራሳቸውን ጥፋት ወይም ስህተት በሌላ ሰው ሲያላክኩ ወይም የተገላቢጦሽ ሲሆን የሚነገር ምሳሌ ነው ። ጽንሰ ሃሳቡ ከጾታ ተጽኖ የመነጨ ነው ፤ ማለት እንድ ኢትዮጵያ  የወንድ የበላይነትና የሴት የበታችነት በሰፈነበት ማህበራዊ ባህልና የፖለቲካ ሥራዓት ባለበት አገር- በባል ጥፋት ሚስት ተወቃሽ ወይም ተጠያቂ ትሆናለች ። ወንዱ ቀኑ ካልቀናው ፣ ጠጥቶ ሰክሮ ፣ ከሰው ተጣልቶ ፣ በአደባባይ ችሎት ሙግት ተሸንፎ ወዘተርፈ ወደ ቤቱ ሲመለስ  ሚስቱን በመደብደብ ወይም በመስደብ ቁጣውን ያበርዳል ።

አቶ ዓለማየሁ እያሱ የሶሻሊስት ጠንቋይ የተሰኘው መጽሐፋቸው ወይዘሮ/ት ሕይወት ታደሰን በመጠቀም አዲስ አበባ በሚገኘው በዋቤሸበሌ ሆቴል ቱባ ቱባ የወያኔ ባለስልጣኖች በተገኙበት አስመረቁ የሚል ዜና ከእትምት/ፕሪንት ድረገጽ ሳነብ ማመን አቃተኝ ። ምክንያቱም ላለፉት ስምንት  ዓመታት ማለት  ኢሕ አ ፓ ለሁለት ከተሰነጠቀበት እ.አ.አ 2007 ዓመት  አንስቶ- አቶ እያሱ  ባገኙትን ዘመናዊ የሚዲያ አውታሮች ሁሉ በመጠቀም ዲሞክራሲያዊ  ኢሕ አ ፓ ዎችን በአንጃነት ፈርጆ- አር እንደነካው እንጨት ሲያስጠይፏችው፣  መስጊድ እንደገባ ውሻ ሲያዋክብዋቸው፣ አገር እንደከዳ ባንዳ ሲኮንንኗቸው ወዘተርፈ ተደምጧል ፤ እየተደመጠም ነው ። ለዚህ ላላሰለሰ ቅስቀሳቸውና ምህረተቢስ ስድባቸው  ዋና ምክንያት- ዲሞክራሲያዊ ኢ. ሕ አ ፓዎች ‘ከወያኔ ጋር ታርቀው አገር ቤት ሊገቡ ነው ‘ የሚል ነው ።

ለካ ለእርሳቸው ያሰቡትን ነው በዲሞክራሲያዊ ኢ ሕ አ ፓዎች ላይ የለጠፉት ። ያ ሁሉ የሃስት ወሬ የነሰነሱትና የስድብ ናዳ ያወረዱት - ምናልባት ካሰቡ እንዳይቀደሙኝ አሸማቅቄ ላስቀራቸው ወይም ላዘናጋቸው በሚል ይሆን ? ስለሆነም ይኸው ባሰሉትና በተዘጋጁበት ወቅት ቀድመው ከወያኔዎች ተቀላቀሉ ። በአካል ባይሆንም በስነልቦና፣ ጭንቅላታቸው ባመረተው መጽሐፋቸው (ኢንተለክቸዋል ፕሮፐርቲ) አማካኝነት እና በሻጭነትና በገዢነት ግንኙነት- ማለት አቶ እያሱ መጽሐፋቸው ሻጭ በመሆን ወያኔዎች ገዢ በመሆን ። ለምን ነበረ አንዳንድ የኢ ሕ አ ፓ አባላት ስለኢ ሕ አ ፓ የደረሱትን መጽሐፍ/ት በአገር ቤት በምሳተማቸው በአቶ እያሱ አለማየሁ የተነቀፉት? ለምሳሌ ስለ ኢ ሕ አ ሠ በጻፈው አስማማው ሃይሉ ላይ ።

ሁለቱ ኢ ሕ አ ፓዎች አብሮ በነበሩበት ጊዜ አሁን ኢ ሕ አ ፓ (ዴ) ወስጥ ካሉት አባላት 'አገር ቤት ገብተን የምንታገልበት መንገድ ለምን አንፈልግም' የሚል ሃሳብ አንስተው እንደነበረና- ሃሳቡም ለጉባኤ ቀርቦ በድምጽ ብልጫ ውድቅ እንድሆነ ከአንዳንድ ከሚቀርቡኝ የኢ ሕ አ ፓ (ዴ) አባላትና ከፓልቶክ ሰምቼውአለሁ ። አገር ቤት ገብተን የምንታገልበት መንገድ እንፈልግ ማለት ፤ አይነገሬ/አይነኬ ባህል( ታቡ) ወይም ወንጀል አድርጎ መመልከት ምን ትርጉም ያሰጣል ? በእኔ እይታ ሦሥት ትርጉም አለው -ይኸወም ፤ (1) በባዕዳን አገሮች ተቀምጦ በመታገል የኢትዮጵያ ሕዝብ ለፖለቲካ ሥልጣን ማብቃት ይቻላል እንደማለት (2) ወያኔዎችን አናስቸግራቸው፤ ጊዜ እንስጣቸው እንደማለት (3) የአባላትን የሃሳብ ነጻነት መንፈግ ወይም መገደብ

'የሶሻሊስት ጠንቋይ' ያሉትን መጽሐፋቸው በዋቤሸበሌ መመረቁን/ላውንች መደረጉን አስመልክቶ ለሚቀርብላቸው ጥያቄዎች የአቶ እያሱ መልስ ምን ይሆን ? እስቲ ልገምት (ስፔኩሌት) ላድርግ ፤ መጽሐፌን ያስመረቀችው ሕይወት ታደሰ እንጂ እኔ አይደለሁም ፤

መጽሐፍ መሸጥና ከወያኔ መታረቅ እየብቻ ናቸው ፤ ሕይወት ታደስ መጽሐፌን በዋቤሸበሌ ሆቴል እንድምታስመርቅ አልነገረችም ፤ የትም ይመረቅ የት እኔ የምፈልገው ገንዘብ ነው ወዘተርፈ ።

ሰውከንቱ ሳያውቀው

29 ጀንዋሪ 2015